**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

# ኢሕአፓ ከአርባ ስድስት ዓመት የህቡዕ ትግል በኋላ

በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ሚና እጅግ የጎላና ብዙ መስዋዕት የተከፈለበት መሆኑ ለብዙዎች ግልጽ ነው። ኢሕአፓ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገርና በሀገራችን ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ታግሎና ሕዝቡን አታግሎ የድሉ ባለቤት ለማድረግ በዓላማ የተንቀሳቀሰ ድርጅት ነው። ይሁን እንጂ በተከታታይ ሥልጣን የጨበጡት አምባገነን አገዛዞች ኢሕአፓን ለማጥፋት ከፍተኛ ጭፍጨፋና ማሳደድ ሲያካሂዱበት ቆይተዋል። ከዚህም የተነሳ የኢ.ሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ ከፊሉ አገር ጥለው ሲሰደዱ ከፊሉ ደግሞ በአገርቤት አቅም በፈቀደ መጠን በህቡዕና በጽናት ሲታገሉ፣ በርካታ አባላቱና ደጋፊዎቹ ደግሞ የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው በትዕግስት ቆይተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ፣ አሳታፊ የፖለቲካ ምህዳር እየፈጠረ መሆኑን በመገንዘብና በዶ/ር አብይ አህመድ የሚመራው መንግሥት ላቀረበው ጥሪ ምላሽ በመስጠት ኢሕአፓ ሀገር ውስጥ ሕጋዊ እውቅና አግኝቶ በይፋ ለመታገል ወስኗል። በዚህም መሠረት በድርጅቱ መሪ በአቶ በላይነህ ንጋቱ ዘለቀ (መርሻ ዮሴፍ) የሚመራ የልዑካን ቡድን (አቶ ጀሚል መሐመድ፣ ዶ/ር ሙሉጌታ ስዩምና ኤንጂነር ሰለሞን ገብረሥላሴ) መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺህ ፲፩ ዓ. ም ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ወደ ውድ ሀገሩ ይመለሳሉ። ስለሆንም ልዑካኑ ሕጋዊ እውቅናን አግኝተው በይፋ ለመሳተፍ ሲገቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሥራ ላይ ያውላሉ፡-

1. ከቦሌ አየር ማረፊያ አቀባበል በኋላ ከተለያዩ የብዙሃን ዜና ማሠራጫዎች ጋር የልዑኩን አባላት በማስተዋወቅ አጭር መግለጫ ይደረጋል። ለጥቆም ልዑካኑን ለመቀበል ከሚገኙ አባላት፣ ደጋፊዎችና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመሆን በቀጥታ ወደ ቀይ ሽብር ወመዘክር ቦታ በመሄድ ለወደቁ ሰማዕቶቻችን የህሊና ፀሎት ይደረጋል። የልዑኩ አባላት የዕለቱን ፕሮግራም አጠናቀው ወደተዘጋጀላቸው ማረፊያ ሥፍራ ያቀናሉ።

2. በተከታታይ ቀናትና ሳምንታት ከአቀባበል ኮሚቴውና ከሌሎች አባላት ጋር በመመካከር በሚያዘጋጀው መርሃ-ግብር መሠረት ልዑካኑ ተከፋፍለው በቀይ ሽብር አደጋ የህሊናና የአካል ጉዳተኞችን ይጎበኛሉ፣ ያጽናናሉ፣ በቋሚነት ከጉዳተኞቹ ጋር የሚያቀራርብ ንዑስ ኮሚቴ ያቋቁማሉ።

Phone : 0039035213311 00393297846515 Email:eprp@eprp-ihapa.com

3. ልዑካኑ ሀገር ውስጥ ከቆዩት አባሎችና ደጋፊዎች ጋር በተናጠልና በቡድን በሚደረጉ የሃሳብ ልውውጦች ላይ ተመሥርተው፣ ሰፋ ያሉ ስብሰባዎች በተለያዩ ከተሞች የሚዘጋጁበትን ሁኔታዎች እያጠኑ ይተገብራሉ። ያልተዜመላቸው የተሰዉ የኢሕአፓ ጀግኖችን ገድል የሚዘከርበትን መንገድ ይመረምራሉ። ይህንንም ጉዳይ ወደ ሚመለከተው የተግባር ኮሚቴ ይመራሉ።

4. ልዑካኑ ፈቀደኛ ከሆኑ የቀድሞ አባላትና በአመለካከት ከሚቀራረቡዋቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር በቀጣዩ ሚናው ላይ ውይይት ያደርጋሉ።

5. ጠ/ሚ አብይ አህመድ ዋሽንግተን በተገኙበት ወቅት ለኢሕአፓ ልዑካን በገቡት ቃል መሠረት ክቡርነታቸውንና ሌሎችንም የመንግሥት ባለሥልጣኖች በማግኘት በጠፉና መዳረሻቸው ባልታወቁ ጓዶቻችን እንዲሁም በሀገራችን የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በማጠናከር ዙሪያ ውይይት ለማድረግ ታቅዷል።

6. ልዑካኑ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ኅብረቶች/ቅንጅቶች አመራር አባላት ጋር በመገናኘት ትውውቅና የሃሳብ ልውውጦች ይደረጋሉ፣ የሀገራችንን የፖለቲካ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት መደረግ ስላለባቸው ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን ስለሚመከርባቸው መድረኮች፣ ዘዴዎችና የሃሳብ ልውውጦች ይደረጋሉ።

**የኢሕአፓ ታሪክ ባጭሩ ምን ይመስላል?**

ኢሕአፓ ዛሬ የሶሻል ዴሞክራሲ ፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያራምድ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜም በመርሆዎቹ ላይ አሰፈላጊውን ማሻሻያ እያደረገ የተጓዘ ፓርቲ ሲሆን፣ የተመሠረተው እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1964 ዓ. ም እንደ ማርክሲስታዊ ፓርቲ ነበር። ፓርቲው ራሱን በይፋ ያወጣው የ1967 ዓ. ም የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳ (በ1966 ዓ.ም.) አንድ ዓመት በኋላ ነው። በሦስቱም ሥርዓት-መንግሥቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በይፋ እንዳይንቀሳቀስ ህልውናው የታገደ ፓርቲ ስለነበረ ለ46 ዓመታት በህቡዕ ለመሥራት ተገዶ ቆይቷል።

ከ1967 ዓ. ም እስከ 1970 ዓ. ም ድረስ ኢሕአፓ በአገሪቱ ውስጥ ከነበሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ታላቁ ነበር። ያንን ግዝፈት ሊያገኝ የቻለው በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ራዕዩንና መርሃግብሩን ስለተቀበሉት ነበር። ለአብዛኛው በድህነት ይኖር ለነበረው ሕዝብ የመሻሻል፣ የእኩልነት፣ የፍትኅና አንድነቱን ጠብቆ በሠላም የመኖር ተስፋ በመስጠቱና ሀገሪቱም ዕድገትና ብልጽግና እንድታገኝ ግዙፍ ዓላማ አለው ብለው ስላመኑ ነበር። ሕዝብ ካመነ ደግሞ ይደግፋል። የኢሕአፓ አባሎች በቅንነት፣ በከፍተኛ የወገንና የሀገር ፍቅር ለለውጥ የቆሙ ታጋዮች ነበሩ/ናቸው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግሮች የራሳቸው ችግር አድርገው የተነሱ፣ ምሁራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የፋብሪካ ላብአደሮች (ያኔ ጥቂቶች ቢሆኑም)፣ አርሶአደሮች፣ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ነጋዴዎችን፣ ልዩ ልዩ ባለሙያዎችን፣ ወታደሮችና በግል ሥራ ተዳዳሪ የነበሩትንም ሁሉ

ያካተቱ ነበሩ። ሴቶችን በማኀበራዊ ፍትኅ ጥያቄዎች ዙሪያና በፆታ እኩልነት ጥያቄ ዙሪያ፣ በአባልነትና ደጋፊነት በብዛት ያሳተፈ የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ነበር። አባሎቹ ከመላው የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የተውጣጡ ለተሻለች ኢትዮጵያ የታገሉና የሚታገሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

ኢሕአፓ የታገለላቸውና አሁንም የሚታገልላቸው ዋና ዋናዎቹ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው። የኢኮኖሚው መሠረት እርሻ በሆነበትና አምራቹ አርሶአደር ግን በጭሰኝነት በሚኖርበት ሀገር፣ የመሬት ሥሪቱ እንዲለወጥ የሚቀርበው ጥያቄ ያለጥርጥር የበርካታው ሕዝብ ድጋፍ የነበረው ነው። ስለሆነም "መሬት ለአራሹ" የሚለውን ጥያቄ አንግቦ ያ ትውልድ በመባል የሚታወቀው በሙሉ ታግሏል። ለኢሕአፓ አባላትም አንኳር ጥያቄያቸው ነበር።

ከወታደራዊ አምባገነንነት ወደ ሕዝባዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር ለመሻገር "ሕዝባዊ መንግሥት" ብሎ ታግሏል፣ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ያለገደብ ብሏል፣ የብሄሮችና የሃይማኖቶች እኩልነትና መብት እንዲታወቅ ታግሏል፣ የኤርትራ ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ወትውቷል።

ከ1969 ዓ. ም እስከ 1973 ዓ. ም ድረስ ፓርቲው ከፍተኛ ጭፍጨፋ፣ የአባሎች ሞት፣ እሥራትና ስደት ደርሶበታል። ቀይ ሽብር እየተባለ በሚጠራውና ነፃ እርምጃ ተብሎ በሚታወቀው የብዙሃን ድምሰሳ፣ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አባሎቹ ተገድለዋል፣ የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችም ሆነዋል። ፓርቲው ራሱን ከጥቃት ለመከላከል የወሰደው እርምጃ ከድርጅቱ አቅም በላይ ከታጠቀ ከመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ጋር ወደ ሰፊ ግፍጫ አደገ። በከተማ ውስጥ የተደረገ ግብግብ በኢሕአፓና በሠላማዊ ሕዝቡም ላይ ትልቅ ጉዳት አስከተለ። ኢሕአፓ ከከተማ ግብግብ ይልቅ መዋቅሮቹን ወደ ገጠር በጊዜው አለማሸሹ ጥፋት እንደሆነ አምኖ ራሱን ወቅሷል፣ በዚህም ለደረሱ ጥፋቶችም በጽኑ ያዝናል፣ ተጸጽቷል።

ቀይ ሽብር ሰብዓዊነትን፣ ኢትዮጵያዊ ባህልና ትውፊትን፣ ቤተሰባዊና ወገናዊ ትሥሥሮችን፣ መተሳሰብንና መተዛዘንን ጭምር ከመሠረቱ የናደ ክስተት ነበር። ሽብሩን ለማምለጥ የቻሉ ኢትዮጵያውያን በአራቱም የዓለም ማዕዘናት የተሰደዱበት፣ በሄዱባቸውም አንዳንድ አገሮች ለከባድ ውርደትና ችግር የተዳረጉበትን ሁኔታም አስከትሏል። አሸባሪው መንግሥት፣ ልጆቻቸው የተገደሉባቸውን ወላጆች የጥይት ዋጋ ከፍለው የልጆቻቸውን ሬሣ እንዲወስዱ ያስገደደበት ሰብዓዊ ዝቅጠት ተፈጥሮም ነበር። የደርግ መንግሥት ወላጆች በየባህላቸው መሠረት ሃዘናቸውን አልቀሰው እንዳይወጡ የከለከለና የልጆቻቸውን ሬሣ ሁለት ሦስት ቀናት በጠራራ ፀሐይ አስጥቶ፣ ሬሣው ላይ መፈክሮችን በሚስማር መትቶ እጅግ ዘግናኝ አረመኔነትን ያሳየበት አሳዛኝ ክስተት ነበር።

ደርግ ኀብረብሄራዊውን ኢሕአፓ በአረመኔነት ሲያጠቃ፣ የጎሣ ድርጅቶች በየአቅጣጫው እየተፈጠሩና እያደጉ ከዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ የተለወጠበት ታሪክ ተፈጥሯል። ከእነዚህ ውስጥ ጉልበት እያገኙ ያደጉት ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት)ና የኤርትራ ሕዝባዊ ግንባር (ሻዕቢያ) ነበሩ። ህወሓት ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዓላማ አንግቦና በመርሃ-ግብሩም ነድፎ ይንቀሳቀስ ስለነበረ፣ ትግራይ ውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረውን የፓርቲውን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ)ን ትግራይን ለቅቆ እንዲወጣ በመጠየቅ፣ ፓርቲውን "አባይ ኢትዮጵያ" (ታላቋን ኢትዮጵያ የሚሹ) እያለ እየተሳለቀበት፣ የትግራይ የኢሕአፓ አባላቱን “ኮራኩር አምሃራ" (የአማራ ቡችሎች) እያለ እየተሳደበ፣ በኋላም ሠራዊቱ ሳይዘጋጅ በማጥቃት የጠባብ ብሄርተኝነት ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ውጊያውን ጀመረ። በዚህም ሳያቆም እየተከታተለ በወልቃይትና በፀለምት፣ ገፍቶም በጎጃም ውስጥ በነበረው የድርጅቱ ሠራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ። ህወሓት አዲስ አበባ ላይ ሥልጣን በያዘ ማግሥት ጀምሮ የኢሕአፓን የከተማ መዋቅሮችን መደምሰስና አባሎችን በመግደል ደርግ ካቆመበት በመቀጥል ምንጠራና ግድያውን ቀጠለ።

ኢሕአፓ በፖለቲካው አውድማ ድምፁ እንዳይሰማም አደረገ። ደርግ በኢሕአፓ ላይ ለ17 ዓመታት የጫነው ሕግ-ወጥነት በመቀጠል ህወሓት/ኢህአዴግም 27 ዓመት ሙሉ አግዶን ቆየን። ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ከምሥረታው ጀምሮ ለ46 ዓመቶች ታግዷል። በነዚህ ዓመታት ፓርቲው በህቡዕ በመንቀሳቀስ እጅግ ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ህልውናውን አስረጦ፣ የሰላምና የመድበለ-ፓርቲ ፖለቲካ በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ያለማቋረጥ ታግሏል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲህ የተስፋ ጭላንጭሎች ስለሚታዩ፣ ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ውስጥ በህጋዊነትና በይፋ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ተዘጋጅቷል። የማኅበራዊ ፍትህን አጀንዳ በማንገብ፣ በሀገራችን ውስጥ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያለፍራቻና አድልዖ እንዲኖሩ፣ ለህግ የበላይነት መስፈን፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለፆታ እኩልነት፣ ለአካባቢ አየር፣ አፈርና ውሃ ጥራትና ተጠቃሚነት፣ ለሥራ አጦች ሥራ በመፍጠርና በሀገራችን ውስጥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የአገራችን አንድነት እንዲጠበቅ…ወዘተ ለመታገል ቆርጦ ተነስቷል።